# ወሳሳ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር

## የባለአክሲዮኖች 29ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

### እአአ የ2023/24 ዓመት አፈጻጸም
### የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

ታህሣስ 17 ቀን 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መልዕክት

## የተከበራችሁ ውድ ባለአክሲዮኖች፣ የኩባንያችን ማኔጅመንትና የኩባንያችን የውጭ ኦዲተር ተወካይ፣

## ክቡራትና ክቡራን፣

በቅድሚያ፤ እንኳን ለወሳሳ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ 29ኛው ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሰላም መጣችሁ እያልኩ፤ የኩባንያውን 29ኛ ዓመታዊ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትን ሳቀርብ የሚሰማኝን ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ:: በሃገሪቱ የተለያዩ ቦታ ተከስቶ የነበረው አለመረጋጋት ቀድሞ የነበረው ዓመት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሮ የቆየ ሲሆን በአጠቃላይ የአፈጻጸም ውጤቱንም መጉዳቱ ይታወሳል:: በዚህ ዓመት አፈጻጸም የተመዘገበው ውጤት ወሳሳ ቀድሞ ካጋጠመው አስቸጋሪ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ተላቆ ወደ ውጤታማ ጎዳና መመለስ መቻሉን የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በአጠቃላይ ወሳሳ የላቀ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን እና የሚያጋጥሙት ችግሮችን በራሱ ተቋቁሞ ማለፍ የሚች ጠንካራ ተቋም መሆኑን ያስረዳል:: በዚህ አጋጣሚ ወሳሳ እንዲህ አይነት አቅም እንዲጎናጸፍ ላደረጉ የማህበሩ ባለአክሲዮኖችን፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ የወሳሳን ማኔጅመንት እና መላው ሰራተኞችን፣ እንዲሁም መላው የወሳሳን ደንበኞች በራሴ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ ስም ላመሰግን እወዳለሁ:: በተለይም ሁልጊዜ በቅርበት እየተከታተለ አስፈላጊውን እገዛ ለሚያደርግልን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያለኝን ምስጋና እያቀረብኩ በመጨረሻም ከወሳሳ ጋር አብረው ለሚሰሩ አጋር ድርጅቶች እና ባለድርሻ አካላት ያለኝን ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ::

# እአአ የ2023/24 ዓመት አፈጻጸም የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

የኩባንያችን የዳይክተሮች ቦርድ ባለፈው አመት የሂሣብ ዘመን 9 ጊዜ የተሰበሰበ ሲሆን የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል።

- ✓ የተለያዩ ፖሊሲዎችን፣ አካሄዶችን፣ መመሪያዎችን እና ማንዋሎችን ከኩባንያው የረዥም ጊዜ ፍላጎት ጋር በማጣጣም አጽድቆ ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርጓል፣
- ✓ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ወሳሳን በዘርፉ ተወዳዳሪ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት አቅራቢ የሚያደርገውን የስትራተጂክ ቢዝነስ ፓላን አጽድቋል፣
- ✓ በየሩብ ዓመቱ የኩባንያውን አፈፃጸም ሪፖርቶችን፣ ለአጠራጣሪ ብድር የተያዘ መጠባበቂያ (Loan Loss Provision) የሚውለውን የገንዘብ መጠን እየገመገመ አጽድቋል፣
- ✓ የደንበኞች የቁጠባ ገንዘብ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ የወለድ ምጣኔዎችን በመከለስ አጽድቋል፣
- ✓ ለወሳሳ ሥራ ማስፋፊያ የሚሆን ገንዘብ ከባንኮች በብድር እንዲወሰድ ፈቅዷል፣
- ✓ ወሳሳ በሚሰራባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች የተከሰተው ያለመረጋጋት ያስከተለውን ተጽዕኖ በመገምገም፤ በነዚህ አካባቢ የሚሰጠው አገልግሎት በወሳሳ ላይ ተጽዕኖ በማይፈጥር እና ለደንበኞች ምቹ በመሆነ መንገድ እንዲመራ አቅጣጫ አስቀምጣል፣
- ✓ ወሳሳን የሚጠቅሙ የኢንቨስትመንት ውሳኔዎችን በተለይም የኮር-ማይክሮፋይናንሲንግ ሲስተሙን፣ የኤጀንት ማይክሮፋይናንሲንግ ሶሉሽኑን፤ የሞባይል ዋሌት አፕልኬሽኑን፣ ከወለድ ነፃ አፕሊኬሽኖችን እንዲዘምኑ ውሳኔ አስተላልፏል

# 1. ዋና ዋና የሥራ አፈፃፀም (ኦፐሬሽናል ፐርፎርማንስ)

## 1.1. የቁጠባ ገንዘብ

የፋይናንስ ተቋማት ትርፋማነት ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሀብት ማሰባሰብ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም የተሻሻሉ የሀብት ማሰባሰብ አቅምን ለማጎልበትና መሰረት ለመጣል ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረትና ትኩረት ተሰጥቶ የቁጠባ ገንዘብን ከማህበረሰቡ ማሰባሰብን ጨምሮ የተለያዩ ተግባራትን ማለትም አስፈላጊ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችንና መሠረተ ልማቶችን በማጎልበት፣ በሁሉም ቅርንጫፎች በቂ፣ የሰለጠኑና ብቁ ባለሙያዎችን ማሰማራት እና ሌሎች በዓመቱ የተቀማጭ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚረዱ ተግባራት ተከናውነዋል።

በእነዚህ ጥረቶች ምክንያት ወሳሳ እ.ኤ.አ ጁን 30 2024 በተጠናቀቀው የስራ ዘመን አጠቃላይ የተቀማጭ ገንዘብ ብር 512,604,007.00 ብር ማሰባሰብ ችሏል። ይኸውም መጠን በብድር የተሰጠቀውን ገንዘብ 43 በመቶ የሚይዝ ሲሆን፤ ቀድሞ ከነበረው ዓመት በብር 22,233,326.00 ይበልጣል። በሌላ በኩል የቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር 242,335 የደረሰ ሲሆን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃር የ19,191 ዕድገት አሳይቷል። ይህም ወሳሳ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ተደራሽነትና የህዝብ አመኔታ እያደገ መምጣቱን የሚያሳይ ውጤት ነው።

## 1.2. ብድር

በተጠናቀቀው የሂሣብ ዘመን ወሳሳ ለደምበኞች የሰጠው አጠቃላይ ብድር መጠን ብር 831,827,614 ደርሷል። ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃር ብር 171.6 ሚሊዮን ቀንሷል። በሌላ በኩል በደንበኞች እጅ ያለው የብድር ገንዘብ ብር 1,186,447,718 ሲሆን ይኸውም ካለፈው በጀት ዓመት በንጽጽር የብር 34.5 ሚሊዮን ቅናሽ አሳይቷል። በሌላ በኩል ወሳሳ ከተመሰረተ ጀምሮ ለደንበኞቹ የሰጠው አጠቃላይ የብድር መጠን ብር 7.4 ቢሊየን ደርሷል።

### 1.3. አነስተኛ የህይወት ኢንሹራንስ (Credit Life Insurance)

ማህበሩ ለደንበኞች ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ የሆነው አነስተኛ የህይወት ኢንሹራንስ (Credit Life Insurance) ተመልክቶ በሂሣብ ዓመቱ የአረቦን ገንዘብ ብር 1,334,289 ተሰብስቧል፡፡ በአንጻሩ በበጀት ዓመቱ ለሞቱ 53 የወሳሳ ተበዳሪ ደንበኞች ዕዳ ብር 787,730 የተከፈለ ሲሆን በዚህም ሰበብ ወደ ወራሾች ሊሄድ የሚችለውን ዕዳ ለማስቀረት ተችሏል፡፡

## 2. የፋይናንስ ክንውን

### 2.1. ሀብት

እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2024 በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የወሳሳ ጠቅላላ ሀብት ብር 1,505,285,608.00 የደረሰ ሲሆን፣ ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃር በብር 25,766,996 ቀንሷል፡፡ ከዚህም የወሳሳ ጠቅላላ ሀብት ውስጥ የደንበኞች የቁጠባ ገንዘብ 512,604,007፣ ከባንኮች የተወሰደ ብድር ብር 617,512,862፣ ያልተከፋፈለ ትርፍ 188,062,339፣ ስጦታና ሌሎች ገቢዎች ብር 70,242,841 ነበር፡፡

### 2.2. ካፒታል

በዓመቱ መጨረሻ የወሳሳ አጠቃላይ ካፒታል ብር 297,122,631 ደርሷል፡፡ ይህም ባለፈው በጀት ዓመት ተመሣሣይ ወቅት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር በብር 62,153,813 ጭማሪ አለው፡፡

### 2.3. ገቢ

በበጀት ዓመቱ ወሳሳ ብር 348,272,201 ገቢ ያገኘ ሲሆን ይህም ባለፈው ዓመት ከተገኘው የገቢ መጠን ጋር ሲነፃር የብር 71,591,986 ጭማሪ ተመዝግቧል፡፡ በበጀት ዓመቱ በስጦታ የተገኘው የጥሬ ገንዘብ መጠን ብር 4,996,825 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

### 2.4. 2.4. ወጪ

በበጀት ዓመቱ ለአጠራጣሪ ብድር መጠባበቂያ የተያዘ የገንዘብ ወጪ ብር 39,334,931 ሲሆን የወለድ ወጪ ደግሞ ብር 102,639,137 ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ በጥቅሉ የሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም ክፍያ፣ የቢሮ ኪራይ እና የቢሮ ዕቃዎች ግዥ ወጪዎች የወጪው

### 2.5. ትርፍ

ወሳሳ በበጀት ዓመቱ በነበረው አፈጻጸም ብር 57,152,184.02 ትርፍ ለማስመዝገብ ችሏል።

## 3. የሰው ሀይል

እ.ኤ.አ. ሰኔ 30 ቀን 2024 በተጠናቀቀው በበጀት ዓመት የተፈጸመው አዲስ ቅጥር ስምንት ሲሆን፣ የተዘጉ የንዑስ አገልግሎት መስጫ ማዕከል ሰራተኞችን ጨምሮ 90 ሰራተኞች ከወሳሳ ለቀዋል። በመሆኑም የወሳሳ ጠቅላላ ሠራተኞች ቁጥር የጥበቃና የፅዳት አገልግሎትን አካቶ 443 ሆኗል። በተጨማሪም በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የወሳሳ ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ በወሳሳ ውስጥም ሆነ ከወሳሳ ውጪ በተዘጋጁ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችና የሥራ ላይ ልምምድ ለ291 ተሳታፊዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን ለዚሁም ብር 729,100 ወጪ ተደርገዋል።

## 4. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ወሳሳ በዘመናዊ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ በመታገዝ የፋይናንስ አካታችነትን በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ የኮር-ማይክሮፋይናንሲንግ ሲስተሙን እና አፕሊኬሽኖችን (የኤጀንት ማይክሮፋይናንሲንግ፣ ኢንተርኔት ማይክሮፋይናንሲንግ፣ ሞባይል ዋሌት እና ከወለድ ነጻ ማይክሮፋይናንሲንግ አፕሊኬሽኖች) ለማዘመን እና ተጠቃሚ ለመሆን የሚረዱ አስፈላጊ ቅድመ ስራዎች የተሰሩ ሲሆን፤ ይህንኑ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከሚያቀርብ ድርጅት ጋር ስምምነት ላይ ተደረሷል።

## 5. የወደፊት ተግባራት

ወሳሳ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የሥራ ዘመን በተለያዩ የስራ ዘርፎች አፈፃፀሙ ወደ ከፍታ የተሸጋገረበት ዓመት ነበር። ደንበኞች በወሳሳ ላይ ያላቸው አመኔታ መጨመር እንዲሁም ሰራተኞች እና ማኔጅመንቱ በግል እና በጋራ ያደረጉት ያላሰለሰ ጥረት ለዚህ ውጤታማ ጉዞ የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል። ይህ ተነሳሽነት እና አመኔታ ወደፊትም እንደሚቀጥል ይታመናል።

በዋና ዋና የስራ ዘርፎች የታየውን እድገት በመጪው ዓመት የበለጠ አጠንክሮ ለማስቀጠል በደንበኞች የቁጠባ ገንዘብ ማሰባሰብ፣ በበኢንፎርሜሽ ቴክኖሎጂ ዘርፍ፣ በሰው ኃይል ልማት፣ እና ካፒታል ማሳደግ ሥራዎች ባለድርሻ አካላት የሆኑትን የወሳሳ ባለአክሲዮኖችን፣

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ ማኔጅመንቱን እና የመላ ሠራተኞችን እና ሌሎች የባለድርሻ አካላትን ጥረት የሚጠይቅ ነው።

## 6. የትርፍ አደላደል

በበጀት ዓመቱ አፈጻጸም የተገኘው ትርፍ ብር 57,152,184 እንደተለመደው ባልተከፋፈለ ትርፍ ላይ ተደምሮ ወሳሳ አገልግሎቱን እንዲያስፋፋበት ጠቅላላ ጉባዔው እንዲወስን የዳይሬክተሮች ቦርድ ሃሳቡን በአክብሮት ያቀርባል።

## ምስጋና

በመጨረሻ በዳይሬክተሮች ቦርድና በራሴ ስም ያላሰለሰ ድጋፍ ላደረገልን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ለወሳሳ ባለአክሲዮኖች እና በእኛ ላይ አመኔታ ጥለው አብረውን ለሚሰሩ ደንበኞች ሁሉ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ያለኝን አድናቆትና ምስጋና እገልፃለሁ። በተጨማሪም ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ ለማኔጅመንቱና ለሁሉም የወሳሳ ሠራተኞች በተለይ ያለፍንባቸው ተግዳሮቶች ሳይበግሯቸው ይህን ውጤት በማስመዝገባቸው ያለኝን ታላቅ አድናቆት እና ምስጋና ስገልፅ ደስታ ይሰማኛል።